# ጤፍ እንኳን ባቅሟ !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



ትንሿ የ'ሕል ዘር፤
ዐይን እንኳ ብትገባ የማትቆረቁር፤
ድንገት ጠብ ብትል የማትገኝ ከምድር፤
ቁልቁል አሾልቃ በንቀት እያየች፤
በድሃው ወገኔ ከት ብላ ሳቀች !
........ እጅጉን አሾፈች ::

አሹቅህን አውልቅ - ሽንብራህን ቆርጥም፤
ባቄላህን ጠርጥር - በቆሎህን ከርትም፤
እኔን ካሁን ወዲያ እንኳን ልትበላኝ፤
ድንገት በመንገድ ላይ ባይንህም አታየኝ፤
እያለች አፌዘች፤
በወገኔ ሳቀች !.......... በወገኔ አሾፈች !!

አረም እንዳይውጣት - ወፎች እንዳይለቅሟት፤
ካቡን ዙሪያ ከቦ - ከብቶች እንዳይበሏት፤
አጭዶና ከምሮ - በሬዎች ለጉሞ፤
ሲወቃ እንዳልዋለ - ቀኑን ሙሉ ቆሞ_ _ _፤

በመንሽ አበጥሮ - በቁና ለክቶ፤
በሰፌድ አንፍሶ - በስልቻ ከቶ፤
ነቀዝ እንዳይበላት - ብርድ እንዳያጠቃት፤
ወቅቶ በጎተራ - እንዳላስቀመጣት_ _ _፤
አንተ አትቀምሰኝም ! ብላ ኮበለለች፤
ጢያራ ተሳፍራ አማሪካን ገባች::

እየተቁለጨለጭክ - ባይንህ ብትቀላውጥ፤
መልሰህ መላልሰህ - ምራቅህን ብትውጥ፤
እንዳማረህ ይቅር - ከቶ አንተ አትበላኝም፤
ባንተ አፍ ገብቼ - ባንተ ሆድ አላድርም፤
ብላ ጤፍ አፌዘች በወገኔ ሳቀች፤
.......... በወገኔ አሾፈች::

ከድሃው ወግነው የቀሩት በሃገር ፤
ባቄላ በቆሎ ጓያውና አተር፤
ሆኖ አለመታደል - ጓያ እግር ሲሰብር፤
አተር ሆድ ሲወጥር _ _ _፤

እንዲሉ !

ምክንያት ሳይፈጥር - አይጣላም እግዜር፤
ተመስገን ባቄላ ያስተነፍስ ጀመር።

የልመና ስንዴ - እያለ ልምጥ ምጥ፤
እሹሩሩ ቢባል - አይወጣ ከምጣድ፤
ጉልቻ ዘብ ቢቆም! - እሳት ቢንቦለቦል!
ምጣድ እሹሩሩ - ማሰሻ ቢያባብል!
ብጥስጥስ እያለ - ኩርፊያውን ማን ሊችል ?!
ከመሰቅሰቂያ ጋር አንስቶ አምባጓሮ፤
ከምጣድ ሳይወጣ ቀረ ሆኖ እንኩሮ ።

የጎደለበትን፤ ቀን የጣለውን ሰው፤
ጤፍ እንኳን ባቅሟ አየኋት ስትንቀው፤
ከፍ ዝቅ አድርጋ ስትገላምጠው፤
ስታበሻቅጠው።

ጤፍ እንኳን ባቅሟ !

በኑሮ ውድነት የተነሳ፤ ጤፍ መብላት እንደሰማይ ለራቃቸው ወገኖቼ ማሸታወሻ ትሁንልኝ።

ሃምሌ 17/ 2007 ዓ.ም ( July 24/2015)